የፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ

# ሳምንታዊ ጋዜጣ

Purpose Black ETHIOPIA

2015 ሀምሌ ቅጽ 1 ቁጥር 18

## ፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ በ3.5 ሚሊዮን ብር ተመን ለ 15 ቀናት የሚቆየውን ሁለተኛ ዙር የTSM ፕሮጀክት አክሲዮን ሽያጭ ማስጀመሩን አበሰረ።

ፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ በታወር ሼር ሆልደር ሞዴል አክሲዮን ሥርዓት ሁለተኛውን ዙር የማስታወቂያ ሽያጭ ዘመቻ ከሐምሌ 1-ሐምሌ 16 2015 ዓ.ም ባሉት 15 ቀናት ለ750 ዕድለኞች ብቻ እንደሚያከናውን ገለጸ።

የኩባንያው ዋና ሥራ አስፈጻሚ ዶ/ር ፍስሐ እሸቱ እንደገለጹት ደንበኞች አክሲዮን በመግዛት የቤት ባለቤት ለመሆን የሚያስችላቸውን ይህን ዕድል በቅድሚያ 3 ሚሊዮን ብር ከፍለው ቀሪውን 500 ሺህ ብር በ5 ዓመታት የጊዜ ገደብ መፈጸም እንደሚችሉ አስታውሰዋል።

ቀደም ሲል ከግንቦት 21 እስከ ሰኔ 6 ቀን 2015 ዓ.ም ለ1000 ዕድለኞች ያዘጋጀውን የመጀመሪያ ዙር የ1.5 ሚሊዮን ብር የማስታወቂያ አክሲዮን ሽያጭ በ8 ቀናት ውስጥ በስኬት ማጠናቀቅ የቻለው ኩባንያችን ፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ አክሲዮኑን ለገዙት ዕድለኞች በቅርቡ የኩባንያው አጠቃላይ ካፒታል 5 ቢሊዮን ብር ሲገባ በ3 እጥፍ ከሚያድገውና የፐርፐዝብላክ ባለቤት ከሚያደርጋቸው የ1.5 ሚሊዮን ብር አክሲዮን በተጨማሪ በመሃል ሜክሲኮ 100 ካሬ ሜትር ይዞታ ላይ የሚያርፍ የባለ ሦስት መኝታ መኖሪያ ቤት የሚያገኙበትን ልዩ ዕድል ተጠቅመዋል።




ፐርፐዝብላክ ኢቲኤች ሰማይ ጠቀሱንና ዓለም አቀፍ መስሕብ የሚሆነውን ታላቁን የከገበሬውን ታወር እንዲሁም በታወር ሼር ሆልደር ሞዴል ፕሮጀክት ሥር የሚገነባቸውን ለመኖሪያ፣ ለንግድ፣ ለመዝናኛና፣ ለቢሮ አገልግሎት የሚውሉ ታላላቅ ሕንጻዎች ሊገነባበት በጨረታ ያሸነፈውን በቢጂአይ ባለይዞታነት ይተዳደር የነበረ በመሃል ሜክሲኮ የሚገኝ ይዞታ ቅድመ ክፍያ 1 ቢሊዮን ብር ከፍሎ መፈጸሙንም አብሥሯል።

ፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ በTSM የአክሲዮን ሥርዓት ያዘጋጀው ሁለተኛ ዙር የማስታወቂያ ሽያጭ ከሐምሌ 1 እስከ ሐምሌ 16 2015 ዓ.ም ባሉት 15 ቀናት የሚካሔድ ሲሆን የአክሲዮን ሽያጭ ዋጋው 3.5 ሚሊዮን ብር ሆኖ በቅድሚያ 3 ሚሊዮን ብር ተከፍሎ ቀሪው 500 ሺህ ብር ክፍያ በ5 ዓመታት የጊዜ ገደብ ከወለድ ነጻ በሆነ አከፋፈል ይከናወናል።

በዚህ ሁለተኛ ዙር የTSM አክሲዮን ሽያጭ አጋጣሚውን ተጠቅመው የሚገዙ ባለ አክሲዮኖች ለታላቁ የከገበሬው ታወር ቅርብ ሆኖ ከታሪካዊው ከገበሬው ታወር አቅራቢያ ከሚገነባውና 8B+G+60 ወለል ከሚኖረው አፓርትመንት ላይ 100 ካሬ ሜትር ይዞታ የሚሸፍን ባለ 3 መኝታ መኖሪያ ቤት በስጦታ የሚበረከትላቸው ይሆናል።

የአክሲዮን ሽያጩ ቀድመው አክሲዮኑን መግዛት ለሚችሉ 750 የዕድሉ ተጠቃሚዎች ብቻ የተዘጋጀ እና በማንኛውም አጋጣሚ ከተቀመጠው ቀነ ገደብ አስቀድሞ ይህ ቁጥር ከተሟላ የ3.5 ሚሊዮን ብር አክሲዮን ሽያጩ ወዲያውኑ ይጠናቀቃል።

## የፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ ፋይናንስ ክፍል አፈጻጸሙን በከፍተኛ ጥራት ለማዳበር የሚስችሉ ዘርፈ ብዙ እንቅስቃሴዎች መጀመሩን አስታወቀ።

የፐርፐዝብላክ ፋይናንስ ክፍል መዋቅሩን በማሻሻል እና አሠራሩን በመከለስ አላስፈላጊ ወጪዎችና ብክነትን ለመቀነስ እንዲሁም የድርጅቱን ገቢ ከማሳደግ አንጻር ተጠቃሽ አማራጮችን ለመጠቀም ከመቼውም ጊዜ በተሻለ በትኩረት እየሠራ እንደሚገኝ የክፍሉ ዋና ኃላፊ አቶ ታደሰ ከበደ አስታወቁ።

ክፍሉ ከዚህ ቀደም በሰነድ አያያዝ እና አቀራረብ የነበረውን ክፍተት በማስተካከል የኩባንያውን የሒሳብ ሪፖርት እና ትንተና ወጥነት ባለው መንገድ ለማስቀጠል እየሠራ ይገኛል ያሉት ዋና ኃላፊው የመረጃ አያያዝ ጥራቱን ለመጨመር ከዚያም ባለፈ ሪፖርቱን ወቅቱን የጠበቀ ለማድረግ ዘርፈ ብዙ እንቅስቃሴዎች መጀመራቸውን ነው የገለጹት።

ምስል በ ነብዩ ዳንኤል



እንቅስቃሴዎቹ በባላንስሺት ሒሳቦች እና በካሽ ፍሎው ሒደት ላይ ሊፈጠሩ በሚችሉ ክፍተቶች ተቋሙን ላልተፈለገ ተጨማሪ የታክስ ወጪ፣ ቅጣት እና ወለድ እንዲሁም ለኦዲት ትችት እየዳይዳረግ በማስቻል ረገድ ጉልህ አስተዋጽዖ እንደሚኖራቸው አቶ ታደሰ ተናግረዋል።

የሒሳብ ምዝገባ ሒደቱንም በተመለከተ በሰለጠኑ የሒሳብ ባለሙያዎች በቴክኖሎጂ በተደገፈ መንገድ የሚያከናውነው ፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ በየበጀት ዓመቱ ማጠናቀቂያ የኩባንያውን ሒሳብ በውጪ ኦዲተሮች እንዲመረመር ዝግጅት እየተደረገ ይገኛል ብለዋል።

በበጀት ዓመቱ መጨረሻ የአላቂ እና ቋሚ ንብረት ቆጠራ በማከናወን ለገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ሪፖርት መደረጉን የተናገሩት አቶ ታደሰ ከበደ ከሒሳብ ኦዲት ጋር በተያያዘም ሪፖርቱን አጠናቅቆ ለኩባንያው ቦርድ እንዲሁም ለጠቅላላ ጉባኤ እንደሚያቀርብ አስታውቀዋል።


ምስል በ ኑበዩ ዳንኤል

> “
> **ዳይሬክተሩ አክለውም ሁሉንም የፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያን የሥራ ዘርፎች እና ክፍሎች በማስተሳሰር ሒሳብን በተቀናጀ መልኩ ለመመዝገብ የሚያስችል የአሠራር ሥርዓት የኢአርፒ ሲስተምን በመዘርጋት ትግበራውን ለማስጀመር ቅድመ ዝግጅቶች እየተደረጉ መሆኑን የተናገሩ ሲሆን ዘመኑ የደረሰባቸውን የፋይናንስ ፕሮግራሞች ተግባራዊ በማድረግ ዘርፉ ላይ ከተሰማሩ ድርጅቶች ጋር በጋራ ለመሥራት እንቅስቃሴዎች መጀመራቸውንም ገልጸዋል።**

የፋይናንስ ክፍሉን በተመለከተ ከኩባንያው ባለድርሻ አካላት ለሚነሡ ጥያቄዎች በሚሰጠው ምላሽ ዙሪያም አብዛኛውን ጊዜ በሥራ ሒደት በሚከናወን የማጣራት ተግባር እና ደንበኞች በሚያቀርቧቸው ያልተሟሉ መረጃዎች ምክንያት በሚከሰተው መዘግየት ክፍተቶች መስተዋላቸውን በመጠቆም የሕዝብ ኃላፊነት እንዳለበት ተቋም ያለአግባብ የሚባክኑ ወጪዎችን መቀነስ እና የሰነዶችን ሕጋዊነት ማጣራት የሚደረግ መሆኑን በማስረዳት ደንበኞችን የማሳመን ሥራ በክፍሉ ኃላፊዎችና ባለሙያዎች እንደሚከናወን አስታውቀዋል።

የተለያዩ የአተገባበር ፖሊሲዎችን በማውጣትና ለሌሎች የሥራ ክፍሎች የፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያን የፋይናንስ አሠራር ሥርዓት ግልጽ በማድረግ የኩባንያውን ገቢ ሊያሳድጉ ይችላሉ ተብለው የተጠቀሱ አማራጮች ተግባራዊ በሚደረጉበት ሒደትም ገንዘብን በአግባቡ በማስተዳደር፣ በገንዘብ አያያዝ እና ተያያዥ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ክፍሉ ድጋፍ እና ክትትል እንደሚያደርግም ተገልጿል።

የኩባንያውን የሒሳብ ሰነዶች አያያዝ ፍሰት ሥርዓት ለማሻሻል የተጀመሩ ሥራዎች ተጠናክረው ይቀጥላሉ ያሉት የፋይናንስ ክፍል ዋና ኃላፊው አቶ ታደሰ ከበደ በቀጣይም ከክፍሉ መደበኛ የሥራ ሒደት ጋር በተገናኘ የሚከናወኑ ሰፊ እንቅስቃሴዎች መኖራቸውን ጠቁመው በክፍሉ የታዩ ክንውኖች አበረታች ቢሆኑም አሁንም የሚስተዋሉትን ውስንነቶች ለመቅረፍ እና የተሻለ አፈጻጸም እንዲኖር ለማስቻል ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች ተለይተው እንደሚሠራባቸው እንዲሁም የከገበሬው ሱቆችን የፋይናንስ ፍሰት በመከታተል ሒሳባቸውን ይበልጥ ወቅታዊ የማድረግ ተግባራት በትኩረት እየተሠሩ መሆናቸውን ተናግረዋል።

ዋና ኃላፊው በመጨረሻም የፋይናንስ መረጃ ማስቀመጫ ማእከልን በማደራጀት እንዲሁም በመጋዘን፣ በከገበሬው ሱቆች እንዲሁም በመስክ ሥራ ላይ የሚገኙ የተቋሙ አላቂ እና ቋሚ ንብረቶች እና ጥሬ እቃዎች አያያዝ ሥርዓት እና የሒሳብ አመዘጋገብ ሒደቶች በኩል ክፍተቶች መስተዋላቸውን በማስታወስ ከኩባንያው ልዩ ልዩ ክፍሎች እንዲሁም ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን የበኩሉን ኃላፊነት ለመወጣት የፋይናንስ ክፍሉ ስትራቴጂ ነድፎ በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛል ብለዋል።

> **የፐርፐዝብላክ የሰው ሃብት ክፍል የሠራተኞችን ማኅበራዊ ትስስር እንዲሁም አቅም እና ክህሎት ለማዳበር ከመቼውም ጊዜ በላይ በትኩረት እየሠራ መሆኑ ተገለጸ።**

> “
> **የፐርፐዝብላክ የሰው ሃብት ክፍል በዋናነት የሠራተኞችን የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ ሙያዊ ሥነምግባርን የተከተለ ከማድረግ በዘለለ የሠራተኞችን አቅምና ክህሎት ከመገንባት አንጻር ብዙ ሰፊ እንቅስቃሴ ማድረግ እንደሚገባው የክፍሉ ዳይሬክተር ወ/ሮ ዘቢብ ሰብስቤ ገለጹ።**

ዳይሬክተሯ የሥራ ቅጥር፣ የዝውውር፣ መልቀቂያ እና ተያያዥ የወረቀት እና የክትትል ተግባራትን ከማከናወን ባለፈ ደንቦችና መመሪያዎችን በማውጣት በኩባንያው የሥራ ክፍሎች እንዲተገበሩ ለማድረግ የሚቻልባቸውን ስልቶች እየነደፈ እንደሚገኝ አስታውሰዋል።

የኩባንያውን የሥራ ባህል እና ተነሣሽነት ለማዳበር የተሻለ አፈጻጸም ላስመዘገቡ ሠራተኞች በተለያዩ ጊዜያት ዕውቅና መሰጠቱን ኃላፊዋ ያነሡ ሲሆን ለአብነትም ለከገበሬው ሱቆች ሠራተኞች እና ማናጀሮች የምስክር ወረቀት እና ማበረታቻ መሰጠቱን ጠቅሰዋል።

ባለሙያ ለሚያስፈልጋቸው የሥራ ክፍሎች በጥያቄያቸው መሠረት ተጨማሪ የሰው ኃይል ከማቅረብ በተጨማሪ ሠራተኞች በተሰማሩበት ዘርፍ ውጤታማ እንዲሆኑ ለማስቻል እንዲሁም የተለያዩ እድገቶች ሲኖሩ ቅድሚያ በመስጠት ተጠቃሚ እንዲሆኑ በርካታ ሥራዎች በመሠራት ላይ ናቸው የተባለ ሲሆን ይህም በአዳዲስ ቅጥሮች ምክንያት የሚወጣውን አላስፈላጊ ወጪ በማስቀረት ረገድ ትልቅ ሚና እንደሚኖረው ተጠቁሟል።

Purpose Black ETHIOPIA

ፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ የሰው ኃይል አደረጃጀቱ ሙያዊ ቅርጹን የጠበቀ እንዲሆን ለማስቻልም የሠራተኞችን የትምህርት ማስረጃ እና የሥራ ልምድ በማየት የበለጠ ውጤታማ ሊያደርጓቸው በሚችሉ ቦታዎች ላይ የመመደብ እና የመደልደል ተግባራት መከናወናቸውን የተናገሩት የክፍሉ ማኔጀር ወ/ት ዓለምፀሐይ አሸኔ ሠራተኞች በመውጫና መግቢያ ሰዓት የጣት አሻራ እንደሚሰጡ እና ሙያዊ ስነ ምግባርን የጠበቀ አለባበስንም ተግባራዊ ከማድረግ አንጻር ሥራዎች መሠራታቸውንም አመልክተዋል።

ወ/ሪት ዓለምፀሐይ አክለውም የሰው ሃብት አስተዳደር ክፍሉ ወርኃዊ የሠራተኞች ስብሰባዎችን ከማድረግ ጀምሮ ለዘርፎች እና ለሥራ ክፍሎች መረጃዎችን በተገቢው ሰዓት እያደረሰ እንደሚገኝ ያስታወቁ ሲሆን በሥራ ሂደት ላይ የሚስተዋሉ የክህሎት ክፍተቶችን በመከታተል ስልጠናዎች እንደሚዘጋጁ ለአብነትም በዋናው መጋዘን እንዲሁም በ፱ዱም ክፍለ ከተሞች በምርት ስርጭት ላይ ሲሠሩ ለቆዩ ወኪሎች ስልጠና መሰጠቱን አስታውሰዋል።

የሰው ሃብት ክፍሉ እንደ ኩባንያው ድጋፍ ሰጪ ከሁሉም የሥራ ክፍሎች ጋር በቅርበት የሚሠራ ቢሆንም ከፋይናንስ፣ ኦዲት እና የሕግ ክፍሎች ጋር በበለጠ በቅርበት እንደሚሠራ የተጠቆመ ሲሆን ከዚህም ጋር ተይይዞ የሕግ ክፍሉ በተለያዩ ጊዜያት የሰው ሃብት ለሚያቀርብላቸው የትብብር ጥያቄ እና ልዩ ልዩ ጉዳዮች ለሚያደርግላቸው ትብብር ምስጋናቸውን አቅርበዋል።

በተያያዘም ከዚህ ቀደም በሠራተኞች ለሥራ መደቦች ብቁ አለመሆን እና በሥራ ኃላፊዎች ትኩረት ማጣት  ምክንያት እንዲሁም በሥራ ሂደት ላይ የሚታዩ የሕግ ጥሰት ክፍተቶችን ለማስተካከል የክህሎት ስልጠናዎችን ጨምሮ በርካታ የመፍትሄ ነጥቦች ተቀምጠው በመተግበር ላይ ናቸው ተብሏል።

ኩባንያው በአሁኑ ወቅት ትኩረት ሰጥቶ በተሰማራባቸው የጥሪ ማእከል፣ የከገበሬው ቴሌቪዥን ጣቢያ እና የከገበሬው ሪልእስቴት ቢሮዎች ግንባታ እና የባለሞያ ማሟላት ሥራዎች ላይ የሰው ሃብት ክፍሉ ከሚመለከታቸው የሥራ ክፍሎች ጋር ተቀራርቦ በመሥራት ላይ መሆኑ ተጠቁሟል።

በመጨረሻም የሠራተኛ ቅጥር ለመፈጸም ከሚደረግ ቅድመ ዝግጅት ማነስ አንስቶ ከሰው ሃብት አስተዳደር ክፍሉ አቅም በላይ የሆኑ እና በበላይ አመራሩ ሊፈቱ የሚገባቸው ጉዳዮች ተለይተው በትኩረት እየተሠራባቸው መሆኑን የተናገሩት ወ/ሮ ዘቢብ ሰብስቤ ክፍሉ የሠራተኞችን ደሞዝ በተመለከተ ከፋይናንስ ክፍል ጋር በቅርበት ከሚሠራቸው ሥራዎች ባሻገር ከሁሉም ዘርፎች ጋር በመናበብና በመቀባበል የኩባንያውን ውጤታማነት ሁለንተናዊ ለማድረግ እንደሚሠራ አስታውቀዋል።

## የፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ ግብርና ክፍል በደሮ እርባታው ዘርፍ ተስፋ ሰጪ እምርታ እያስመዘገበ መሆኑ ተገለጸ።

የኩባንያው የግብርና ክፍል ከሁለት ወራት በፊት ከባስሚን ሞደርን ፖሊትሪ ፋርም ጋር በመቀናጀት በሆለታ ከተማ አዲስ ዓለም አካባቢ በርካታ ቅድመ ዝግጅቶችን በማሟላት የዶሮ እርባታ መጀመሩ የሚታወስ ሲሆን በመጀመሪያው ዙር ካረባቸው 2000 ዶሮዎች ከ300 ያላነሱትን እርዶ ለገበያ ማቅረቡን አስታውቋል።

ክፍሉ ከዚህ ቀደም ለእርባታው 20 ሺህ ዶሮዎችን የመያዝ አቅም ያላቸው 9 ዘመናዊ የዶሮ ቤቶችን በማደራጀት እና 15 ሠራተኞችን በመቅጠር ወደ ትግበራ የገባ ሲሆን ዶሮዎቹም እንደየጊዜያቸውና የእድገት ደረጃቸው የተመጣጠነ ምግብ፣ ንጹህ የመጠጥ ውሃ እንዲሁም ሕክምና እያገኙ ቆይተዋል ተብሏል።

ክፍሉ ደረጃውን በጠበቀ መንገድ አስፈላጊ የሆኑ ቅድመ ሁኔታዎችን በማሟላት የዶሮዎቹን እርድ ማከናወኑን የገለጹት አቶ ሰሎሞን ጥራት ባለው መንገድ በማሸግ በሁሉም የከገበሬው ሱቆች እንዲሁም በዋናው መሥሪያ ቤት ለኩባንያው ሠራተኞች ማቅረቡን ይፋ አድርገዋል።

በዚህ ሳምንትም ተጨማሪ 3500 የአንድ ወር ጫጩቶችን በማስገባት ለመጪው 2016  ዓ.ም የዘመን መለወጫ ሳይታረዱ ለገበያ ለማቅረብ ዝግጅቶች ተጀምረዋል የተባለ ሲሆን በቅርቡም ተጨማሪ 1000 የአንድ ቀን ጫጩቶች ወደ እርባታ ስፍራው እንደሚጨመሩ ተጠቁሟል።



Source - Pinterest

> “
> **በተያያዘ ዜናም በወቅታዊው አየር ለውጥ ምክንያት በተለያዩ አካባቢዎች የጣለው ከባድ ዝናብ በእርሻ ስራው ላይ ቀላል የማይባል ተጽእኖ ማሳደሩን የፐርፐዝብላክ አጠቃላይ እርሻ ሥራ አስኪያጅ (ኦልፋርም ማናጀር) አቶ ሰሎሞን ዓለምሰፋ አስታወቁ።**

ፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ በተለያዩ ክልሎች በግብርና ሥራ በሚያለማቸው እርሻዎች የተለያዩ የአትክልትና ፍራፍሬ እንዲሁም የጥራጥሬ ሰብል ምርቶችን በብዛትና በጥራት በማልማት ለሸማቹ በተመጣጣኝ ዋጋ እያቀረበ የሚገኝ ሲሆን ከጥቂት ወራት ወዲህ በመላ አገሪቱ በጣለው ወቅቱን ያልጠበቀ ዝናብ ምክንያት መስተጓጎል እንደገጠመው ተገልጿል።

በተለይም በኦሮሚያ ክልል አርሲ ዞን በቆጂ በተደጋጋሚ በጣለው ከባድ ዝናብ መሬቱ እጅግ መርጠቡ  በአካባቢው ካለው የአፈር አይነት ጋር ተደምሮ የእርሻ መኪኖችን ለማስገባት እና ለማረስ አዳጋች እንዳደረገው ተጠቅሶ የአፈር ማዳበሪያ አቅርቦትና ሥርጭት እጥረት ለእርሻ ሥራው መስተጓጎል ሌላኛው ምክንያት መሆኑ ተጠቁሟል።

መጠኑ ቢለያይም ተግዳሮቱ በሁሉም እርሻዎች ላይ መከሰቱን ያወሱት ኃላፊው ምርታማነትን ለመጨመር የግብርና ግብዓቶች መሟላት ሰፊውን ድርሻ እንደመያዙ በምግብ ራሳችንን ለመቻል በምናደርገው ንቅናቄ በእርሻ ሥራው ላይ የሚስተዋሉ ተግዳሮቶች የማያዳግም የመፍትሔ እርምጃ ያስፈልጋቸዋል ሲሉ ተናግረዋል።

**ዋና አዘጋጅ፦ ሰላማዊት ደበበ**
**ሲንየር ሪፖርተር፦ ጌታባለው ገ/ሐና**
**ሪፖርተር፦ ኤደን ደነቀ**

**ለበለጠ መረጃ**

ስንጋተራ ነጋዴዎች ህብረት ህንጻ 5ተኛ ፎቅ

+251-946-545454/
+251-925922222/
+251-925822222

7151

www.purposeblackethiopia.com